**በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ ከ4 — 6 ሰዓት ለሚካሔዳው የልጆች መርሐ ግብር በምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል ላሉ ተማሪዎች የተዘጋጀ ሳምንታዊ ትምህርት**

**ምድብ ሦስት (ከ4ኛ — 6ኛ) ክፍል**

**22 ኛ ሳምንት**

**የአሥሩ ደናግል ምሳሌ**

**ዓላማ**

❖ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ መዘጋጀት እንደሚገባን መማር።

**ጥቅስ**

❖ "እነሆ ሙሽራው ይመጣል ትቀበሉት ዘንድ ውጡ።" ማቴ–ስ 25፥6

**መግቢያ**

❖ ያለፈውን ሳምንት ትምህርትና ጥቅስ ማስታወስ።
❖ ልጆች ስለ ጋብቻ በዓል ወይም ሥነ ሥርዓቱ እንዲሁም ስለ ድንግልና ያላቸው ግንዛቤ ምን እንደሆነ ይጠይቋቸው።

**የትምህርቱ መግለጫ**

❖ ጌታችን ብዙ ጊዜ በምሳሌ ያስተምር ነበር። ለምን?
❖ ወደ ሠርግ ስለ ተጋበዙት አሥሩ ደናግል ለሕዝቡ አስተማራቸው።
❖ መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ለመገናኘት ቢወጡም አምስቱ ከሙሽራው ጋር ወደ ሠርጉ ሲገቡ አምስቱ ግን ስለዘገዩ ተከለከሉ።
❖ አምስቱ ልባሞች ኅበሯች ሲሆኑ የተቀሩት አምስቱ ግን ሰነፎች ነበሩ።
❖ ልባሞቹ ከመብራታቸው ጋር ዘይት ይዘው የነበረ ቢሆንም ሰነፎቹ ግን ዘይቱን ትተው መብራት ብቻ ይዘው ነበር።
❖ ሙሽራውም ሲዘገይ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ።
❖ እኩለ ሌሊትም ሲሆን ሙሽራው ይመጣልና ትቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ድምፅ ሲሰማ ውካታ ሆነ።

**ጥያቄ**

1. አምስቱ ድናግል ኅበሯች የተቀሩት አምስቱ ደግሞ ሰነፎች የተባሉት ለምንድን ነው?
2. ሙሽራው ሲዘገይ ሁሉም ምን አደረጉ?
3. እኩለ ሌሊት ሲሆን ሁሉም ምን ገጠማቸው?

❖ ወዲያውም ቆነጃጅቱ ወይም ድናግሉ ሁሉ ተነስተው መብራታቸውን አዘጋጁ።
❖ ሰነፎቹም መብራታችን ሊጠፋብን ነውና ከዘይታችሁ ስጡን ብለው ልባሞቹን ጠየቋቸው።
❖ ልባሞቹ ግን ምናልባት ለእኛና ለእናንተ ስለ ማይበቃ ወደ ሚሸጡት ሄዳችሁ ለራሳችሁ ግዙ አሉአቸው።
❖ ሰነፎቹም ዘይት ሊገዙ ሲሄዱ ሙሽራው በድንገት መጣ። ተዘጋጅተው የነበሩትም ልባሞች ከሙሽራው ጋር ወደ ሠርጉ ገቡ፥ በሩም ተዘጋ።
❖ ሰነፎቹ ቆነጃጅት መጡና ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ ክፈትልን አሉ። እርሱ ግን አላውቃችሁም አላቸው። ❖ ከዚህ በኋላ ጌታችን የተሰበሰቡትን ሕዝቦች ሁሉ ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና ነቅታችሁ ኑሩ አላቸው።

**ጥያቄ**

1. ልባሞቹ ቆነጃጅት እነማን ናቸው? (የተዘጋጁት)
2. ሰነፎቹ ቆነጃጅትስ እነማን ናቸው? (ያልተዘጋጁት)
3. ዘይቱ ምንድር ነው? (ሥራ) ሙሽራው ማነው? (ጌታችን)
4. ለእኛና ለእናንተ አይበቃም ማለት ምን ማለት ነው? (ጻድቅ በጭንቃ ይድናል ማለት ነው።)
5. በሩም ተዘጋ ማለት ምን ማለት ነው? (በፍርድ ቀን ንስሐ ለመግባት የምናደርገው ጥረት ሁሉ ዋጋ ቢስ ነው ማለት ነው።)

**ማጠቃለያ**

❖ ከጌታችን ጋር ዳግመኛ መቼ እንደምንገናኝ ስለ ማናውቅ ዘወትር ተዘጋጅተን ልንኖር ያስፈልጋል።
❖ በሕይወታችን እያንዳንዷን ደቂቃ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን በትክክል በመጠቀም ወደ ጌታችን መቅረብ ይገባናል። በዚህ ሁኔታ ከኖርን ጌታችን ሲመጣ ያውቀናል እኛም ልናውቀው እንችላለን።

**ተግባር**

❖ መጸለይ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ወይም ወደ ቤተክርስቲያን መሄድን ውስጣችሁ የማይፈልግ ከሆነ በትእምርተ መስቀል ምልክት በማማተብና የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ በመፈጸም ይህንን ክፉ ሐሳብ ከእናንተ አርቁ።
❖ አሥር ልጆች በወረቀት በሻማ ልክ የተሰራ የሻማ መሽፈኛ ያዘጋጁ። አምስቱ በውስጡ ሻማ ይኑራቸው፥ አምስቱ ግን ወረቀቱን ብቻ ይዘው ይቅረቡ። ከዚህም በኋላ ልጆቹ የተማሩትን ታሪክ በመምህሩ አጋዥነት በተግባር በቲያትር መልክ ያሳዩት።

**ይቆየን።**

**አዘጋጅ፦ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ          የካቲት ፳፩ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.**